I. ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ መልሱ

1. ምስራቅ አፍሪካን የማያዋስነው የአፍሪካ ቀጣና የቱ ነው?

ሀ. ምዕራብ አፍሪካ ሐ. ማዕከላዊ አፍሪካ

ለ .ሰሜን አፍሪካ መ. ደቡብ አፍሪካ

2.ስለ ኬክሮስ መስመሮች ትክክል የሆነው የቱ ነው?

ሀ. ከሰሜን ወደ ደቡብ የተሰመሩ ናቸው

ለ. ሰሜንና ደቡብ ዋልታ ላይ ይገናኛሉ

ሐ. መነሻቸው የምድር ወገብ ነው

መ. ጠቅላላ ብዛታቸው 360 ነው

3.የአንድን ነገር ፍፁማዊ መገኛ ለማወቅ የማይጠቅመው የቱ ነው?

ሀ. ኬክሮስ ሐ. ኬንትሮስ

ለ. ድልድይ መ. ቋሚ መስመር

4.የተፈጥሮ ሀብቶችን ለመፈለግና ለመንከባከብ የሚጠቅመው የካርታ መፈለጊያና መተግበሪያ የቱ ነው?

ሀ. ጂፒኤስ ለ. ጎግል ካርታ ሐ . ስቴቶስኮፕ መ. ጎግል ኧርዝ

5.የምስራቅ አፍሪካ ስምጥ ሸለቆ በአፍሪካ አህጉር ብቻ ምን ያህል ኪ.ሜ ይረዝማል?

ሀ. 5400 ለ. 5600 ሐ. 7200 መ. 1200

6. ከምስራቅ አፍሪካ ሀገራት የማይመደመው የቱ ነው?

ሀ. ታንዛኒያ ለ.ሞርሽየስ ሐ. ቦትስዋና መ. ሞዛምቢክ

7. ከሚከተሉት ሀገራት መካከል ዝናብ ከሰኔ እስከ መስከረም የሚያገኘው የቱ ነው?

ሀ. ኢትዮጵያ ለ. ታንዛኒያ ሐ. ዚምባብዌ መ. ሞዛምቢክ

8. ስለደም ትክክል ያልሆነው የቱ ነወ?

ሀ. ደም ከደም ህዋሳትና ከፕላዝማ ይሰራል

ለ. ደም ሰውነታችንን ከበሽታ ይከላከላል

ሐ. ደም እንዳይፈሰን ይከላከላል

መ. የደም ህዋሳት ትንሹ አንጀት ውስጥ ይመረታሉ

9.ደም ቅዳዎች ለምን ወፍራም ግድግዳ ሊኖራቸው ቻለ?

ሀ. በኦክስጅን ያልበለፀገ ደም ስለሚያልፍባቸው

ለ. ደምን ከተለያዩ የሰዉነት ክፍሎች ወደ ልብ ስለሚመልሱ

ሐ. ደም በከፍተኛ ግፊት ስለሚያልፍባቸው

መ. ደም መልስንና ቀጫጭንደም ስሮችን ስለሚያገኙ

10. ቁጥራቸው ከፍተኛ የሆነው የደም ህዋሳት የትኞቹ ናቸው?

ሀ. ፕላትሌቶች ሐ. ፕላዝማ

ለ. ቀይ የደም ህዋሳት መ. ቀይ የደም ህዋሳት

11.በኦክስጅን የበለፀገ ደምን ከ _____ተቀብለው ወደ ግራ ተቀባይ ልበ ገንዳ የሚያስተላልፍ የደም ስሮች _____ይባላሉ::

ሀ. ድልሺ/አኦርታ ሐ. ጉበት/ፑልሞናሪ አርተሪ

ለ. ልብ/ቬናካቫ መ. ሳንባ/ ፑልሞናሪ ቨይን

12.አንድ ሰው አደጋ ደርሶበት ደሙ ፈሶ እንዳያልቅ የሚያደርጉት የትኞቹ የደም ህዋሳት ናቸው?

ሀ. ቀይ የደም ህዋሳት ሐ. ነጭ የደም ህዋሳት

ለ. ፕላትሌቶች መ. ሂሞግሎቢን

13. አየር ወደ ውስጥ ስናስገባ :

ሀ. ድልሺ ይወጠራል ሐ. ሳንባችን ይሚሸሻል

ለ. ድልሺ የደጋን ቅርፅ ይይዛል መ. ድልሺ ይረግባል

14. 99% የሚሆነው የአየር ምንዝር ከየትኞቹ ጋዞች የተገኘ ነው?

ሀ. ናይትሮጅንናኦክስጅን

ለ. አርገንና ኦክስጅን

ሐ. ካርቦንዳይኦክሳይድና ናይትሮጅን

መ. ኦኮስጅንና ካርቦንሞኖኦክሣይድ

15. እፅዋት ምግባቸውን ለማዘጋጀት የሚጠቀሙት የአየር ምንዝር የትኛው ነው?

ሀ. የውሃ ተን ሐ. ኦክስጅን

ለ. ካርቦንዳይኦክሳይድ መ. ናይትሮጅን

16. የጨው ሙሙት ስንት ምንዝሮች ይዟል?

ሀ .5 ለ. 3 ሐ . 4 መ . 2

17. የዋህድ ዘር ድብልቅ ምሳሌ የሆነው የቱ ነው?

ሀ. ደም ሐ. የ ጤፍና የስንዴ ድብልቅ

ለ. የአልኮልና የውሀ ድብልቅ መ. ወተት

18. ስለ ድብልቅ ስህተት የሆነው የቱ ነው?

ሀ. የድብልቅ ምንዝሮች ከተጣመሩ በኃላ ማንነታቸውን ይቀይራሉ

ለ. ድብልቅን ለመፍጠር ቢያንስ ሁለት ምንዝሮች ያስፈልጋሉ

ሐ. የድብልቅ ምንዝሮችን በአካላዊ መንገድ መለየት ይቻላል

መ. ድብልቆች ቁስ አካል ናቸው

19. የውሀንና የአልኮል ድብልቅን በየትኛው ድብልቅን የመለያ ዘዴ እንለያለን?

ሀ . ቀረራ ለ. ትነት ሐ. ንጥረት መ. ጥሊያ

20. ታዳሽ የጉልበት ምንጭ የሆነው የቱ ነው?

ሀ. የድንጋይ ከሰል ሐ. ነፋስ

ለ. የማገዶ እንጨት መ. ዩራኒየም

21. ሚስማርን በመዶሻ ለመንቀል የሚጠቅመው የቀላል መኪና አይነት የቱ ነው?

ሀ. ዘንባይ ወለል ለ. ሽክርክሪት ሐ. መፍቻ መ. መፈንቅል

21.በኢትዮጵያ ከፍተኛ ቦታዎች አካባቢ የሚታየው አማካይ አመታዊ የሙቀት መጠን ስንት ነው?

ሀ. 6 ድግሪ ሴንቲግሬድ ሐ. 26 ዲግሬ ሴንቲግሬድ

ለ. 17 ድግሪ ሴንቲግሬድ መ. 24 ደግሪ ሴንቲግሬድ

22. የአየር ንብረት ይዘት ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. አፈር ለ. የሙቀት መጠን ሐ. የአየር ግፊት መ. ዝናብ

23.ከምድር ወገብ ከ 5° እስከ 15° ሰሜንና ደቡብ ንፍቀ ክበብ የሚገኘው የአየር ንብረት ክልል የቱ ነው?

ሀ. የደጋ አየር ንብረት ክልል

ለ. የሀሩር የአየር ንብረት ክልል

ሐ. የበረሀ የአየር ንብረት ክልል

መ. የሳር ምድር ሞቃታማ የአየር ንብረት ክልል

24. ስለ ከፍታና የሙቀት መጠን ዝምድና ትክክል የሆነው የቱ ነው?

ሀ. ከፍታ ሰጨምር የሙቀት መጠን ይጨምራል

ለ. ከፍታ ሲቀንስ የሙቀት መጠን ይቀንሳል

ሐ. ከፍታ ሲቀንስ የሙቀት መጠን ይጨምራል

መ. ከፍታና የሙቀት መጠን ግንኙነት የላቸውም

25. የአየር ንብረት ተቆጣጣሪ ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. ከፍታ ሐ. ከባህር ያለው ርቀት

ለ. ከምድር ወገብ ያለው ርቀት መ. የዝናብ መጠን

26. የጉልበት መለኪያ አሀድ የቱ ነው?

ሀ. ጁል ለ. ኬልቪን ሐ. ሴኮንድ መ. ኪሎ ግራም

27. በመዳብ: ኒኬልና በዚርኮን ማአድናት የምትታወቀው የምስራቅ አፍሪካ ሀገር የቷ ናት?

ሀ . ሩዋንዳ ለ. ሶማሊያ ሐ.ኬኒያ መ. ቡርንዲ

28. ተገቢ ያልሆነ የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም የሆነው የቱ ነው?

ሀ. በወንዞች አካባቢ ዛፍ መትከል

ለ. ባዮጋዝ መጠቀም

ሐ. በቤት ውስጥ ውሀን በአግባቡ መጠቀም

መ. የተፈጥሮ ሀብቶችን ያለ ገደብ መጠቀም

29.በአለም ላይ ካለው የውሀ መጠን ውስጥ በበረዶ መልክ የሚገኘው ምን ያህል ነው?

ሀ. 2 % ለ. 70% ሐ. 1% መ. 97%

30. ከምስራቅ አፍሪካ ሀይቆች በጥልቀቱ የመጀመሪያው የቱ ነው?

ሀ. ኬቩ ለ. ማላዊ ሐ. ታንጋኒካ መ. ኤድዋርድ

31. ዙሪያውን በደረቅ መሬት የተከበበ አነስተኛ የውሀ ክፍል ምን ይባላል?

ሀ . ወንዝ ለ . ውቅያኖስ ሐ. ባህር መ. ሀይቅ

32. የታንዛኒያና የሞዛምቢክ ድንበር በመሆን የሚያገለግለው ወንዝ ማን ይባላል?

ሀ. ዛምቤዚ ለ. ሩቩማ ሐ. ሩፉጂ መ. ታና

33. የቪክቶሪያ ፏፏቴ የሚገኝውበየትኛው የምስራቅ አፍሪካ ወንዝ ላይ ነው?

ሀ. ዛምቢዚ ለ. ዋቢሸበሌ ሐ. ታና መ. ናይል

34. ወደ ህንድ ውቅያኖስ የማይገባው የምስራቅ አፍሪካ ወንዝ የቱ ነው?

ሀ. ናይል ለ. ታና ሐ. ሩቫማ መ. ገናሌ

35 .ለናይል ወንዝ 86% ውሀ የምታበረክተው የምስራቅ አፍሪካ ሀገር ማን ናት?

ሀ. ኬኒያ ለ. ኢትዮጵያ ሐ. ደቡብ ሱዳን መ. ጅቡቲ

36. ከሚከተሉት ሀገራት መካከል ከደንከል በረሀ ጋር የማይዋሰነው የቱ ነው?

ሀ. ኤርትራ ለ. ጅቡቲ ሐ. ኢትዮጵያ መ. ኬኒያ

37.ከቦታ ቦታ በሚዘዋወሩ የዱር እንሰሳት የሚታወቀው የምስራቅ አፍሪካ ስነ ምህዳር የቱ ነው?

ሀ. ማሣይ ማራ ፓርክ ሐ. የቫሩንጋ ተራራ

ለ. የደንከል በረሀ መ. የሰሜን ተራሮች ብሄራዊ ፓርክ

38. ከሚከተሉት መካከል የእፅዋትን አይነትና ስርጭት በቀጥታ የማይቆጣጠረው የቱ ነው?

ሀ. አፈር ለ. ከፍታ ሐ . የዝናብ ስርጭትመ. የህዝብ ብዛት

39. የቅጠለ ሰፋፊ ደን ዛፎች ምሳሌ ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. ወይራ ለ. ቁልቋል ሐ. ጥቁር እንጨት መ. ዋንዛ

40. የቅጠለ አርጋፊ ዛፎች ለምን በበጋ ወቅት ቅጠላቸውን ያረግፋሉ?

ሀ. የውሀ ትነትን ለመቀነስ ሐ. ሀይለኛ ነፋስ ስለሚነፍስ

ለ. የመሬትን ስበት ስለማይቋቋሙ መ. ከፍተኛ ዝናብ ሥላለ